# ቅሌታም ዓረመኔ ምሁራን
# ለአገርና ለኢትዮጵያዊነት
# አሁንም ድረስ ስላላረፉ ማጋለጥና
# አሳዶ መታገል ያስፈልጋል

*ከአስተዋይ በቀለ*

እንደ አብነት የምትታየዋ የእፁብ ድንቅ አገራችንና የአኩሪ ኢትዮጵያዊነታችን ቀንደኛና አክራሪ ባላንጣ መልክተ - ጽልመት የሆኑ ዓረመኔና ቅሌታም ምሁራን ናቸው።

እነዚህ ምሁራን ትምህርትን ለጥፋት ያዋሉ፣ ሀሰትን ተወዳጅተው እውነትን የራቁ፣ ንፁሕ ልብና በጎ ሕሊና የሌላቸው መሰሪና እርኩሳን በመሆናቸው አገራችንና ሕዝባችን ዛሬ የሚገኙበት አስከፊ ሁኔታዎች ላይ ለመውደቅ በቅተዋል።

አይ ምሁር ! የትነው የምትሄደው ሲሉት እንኳ ራሴን ልቆረጥ ነው ይላል። የኢትዮጵያ አምላክ ይቁረጠውና ምን አለበት ፀጉሬን ልስተካከል ነው ብሎ እውነቱን ቢናገር?

እንደ ሙታን ያልነቃና ከብሔር/ብሔረሰብ ቁራኛ ያልተላቀቀ ድንባዣም ምሁር የሰለጠነና ያወቀ መስሎት እንደ ኋላ - ቀር የከሰል ባቡር ጥቁር ጢስ እየተፋ አገርን፣ ኢትዮጵያዊነትንና ሰንደቅ ዓላማን ጥላሸት ይቀባል። ስማ አንተ ምሁር ! አገር ያጠፉና ሕዝብ ያተራመሰ ቅሌት ከሌለብህ አትፍራ።

ነገር ግን ጋዝ ያለበት ዝላይ አይችልምና ለምን ምሁር ተነካ የምትል ከሆነ መንገዱን ጨርቅ ያርግልህ። በአገር፣ በሕዝብና በሰንደቅዓላማ ቀልድ የለምና አንተንም እዚያው ዱለን አብረን እንደ ሊጥ እናሸሃለን እንጂ ዘንድሮ አንለቅህም። በግዜ ንስሃ ገብተህ አቋምክን ከአገር፣ ከኢትዮጵያዊነትና ከሰንደቅ ዓላማ ጋር አስተካክለህ ብትቆም ይሻልሃል።

አይ አውቃለሁ ባይ ድንባዣም ዓረመኔ ምሁር ! እስትንፋሱ ግም፣ አንደበቱ ቅሌት፣ ግሳቱ ጥፋት፣ ጠረኑ ክርፋት፣ ሥራው ክፋት፣ የሚያስበው ትርምስ፣ እይታው ግንጠላ፣ የሚይዘው - የሚጥለው ምስቅልቅል፣ አምላኩ ዲቢሎስ፣ አጎቱ ጋኔን፣ ቤተሰቦቹ አጋንንት፣ ጓደኞቹ እርኩሳን፣ ሚስቱ ጥላቢስ፣ ልጁ ከልብ፣ ልብሱ ግልብጥ፣ ጫማው ወልጋዳ፣ አቋሙ አፍራሽ፣ ባህሪው በጥባጭ፣ ሆዳም፣ ቀላዋጭ፣ አጋሰስ ገና ተምሬአለሁ ብሎ በአገር፣ በሕዝብና በሰንደቅ ዓላማ ላይ ያላግጣል።

ይኸ ከንቱ፣ የከንቱ ከንቱ ድንባዣም ምሁር ቅሌትንና ዓረመኔያዊ ተግባርን በግሃድ ለብሶና ተከናንቦ በኢትዮጵያዊነት ላይ ያሴራል።

ያዳምና ሔዋን ክፋት የተጠናወተው ከይሲ ባንዳ ካለ ጂ.ፒ.ኤስ መኖሪያ ቤቱን ፈልጎ ማግኘት እንኳ የማይችል ብሔር/ብሔረሰብ እያለ አንድነታችን ሳያቋርጥ ይወጋል። ይብላኝ ለዚህ ቅሌታም ምሁር እንጂ ኢትዮጵያዊነት እንደሁ እንደ አንበሳ ሳይፈራ ለዘለዓለም ይኖራል።

ይህ አገር አታራማሽ ሰላቢ የቀላወጣትን ያችን መከረኛ የራስን ዕድል በራስ መወሰን ሐረግን አስር ጊዜ እያነሰ ዛር እንዳለበት ሰው ያጓራል። የኛ ምሁር ተብዬ የመገነጣጠል በሽታህ ካልተወህ የሰፈርህን ዶሮ እያነቀህ ገነጣጥል እንጂ ኢትዮጵያዊነትስ አገሩን አያስቆርስም አፀመ-ርስቱንም አያስነካም።

ቅሌታም ምሁር አልገባውም እንጂ ባዕድ ፍልስፍናና ርዕዮተዓለም ለራሱ ለማርክስም አልሆነውም። ያንን መከረኛ አይሁድ ከአገሩ አሳድዶ የሚበላውንና የሚያጨሰውን አሳጥቶ የአንድ ኃብታም ሸማኔ ተደጓሚ ያደረገው ራሱ የጫረው ፍልስፍና ሲሆን፤ ይኸው ፍልስፍና ኋላ ሌኒንንም ያልጋ ቁራኛ አድርጎ ሸምቅቆ አጠፋው፣ ስታሊንንም ቮድካ እየጋተ ገደለው፣ ትሮትስኪንም ሴሰኛ አድርጎ አሳዶ ደፋው፣ ኃይሌ ፊዳንም ሲጋራውን እያስማገ በኦሮሞ ገበሬ አስገደለው፣ መንግሥቱ ኃይለማርያምንም እጁን በደም ነክሮ አገር አስከዳው፣ ካስትሮንም፣ ያልጋ ቁራኛ አድርጎ አድርቀታል፣ እረ ስንቱ!!

ቅሌታም ምሁር ባዕድ ርዕዮተዓለም እየኮረጀ፣ እየከዳና እየተገዛ እንደ አብነት በምትታየው አገራችን ላይ ቅጥረኛ ባንዳነትና ዓረመኔ ተግባር እየፈጸመ አገራችንንና ሕዝባችንን እየበጠበጠና እያተራመሰ ነው። በየጎራው፣ በየቡድኑ፣ በየስብስቡ ወዘተ.... አሁን ድረስ ለኢትዮጵያ፣ ለኢትዮጵያዊነትና ለሰንደቅ ዓላማችን ያልተኙ አፍራሽ ምሁራን ብዙ ናቸው።

ኢትዮጵያን፣ አንድነቷን፣ ሰንደቅ ዓላማዋን የበደሉ ሁሉ ፍፃሜያቸውን ያገኛሉ።

ስለሆነም እነዚህ ኢትዮጵያዊያን፣ ኢትዮጵያዊነትንና ሰንደቅ ዓላማን ያረከሱ ቅሌታም ምሁራን በእግዚአብሔር ቁጣ በእሳት ፍላፃ በያሉበት ተወግተው እንደሚጠፉ በቅዱስ መንፈስ ተገልጿል።

የኢትዮጵያም ሕዝብ በበኩልህ አንድ አገር፣ አንድ ሕዝብ፣ አንድ ሰንደቅ ዓላማ አርማህንና እምነትህ ይዘህ ቅሌታም ባንዳ ምሁራንን አሳደህ ታገል ! አጋልጥ ! ጭንቃቸውንም አብዛው ! ጊዜው አሁን ነው ድሉ ያንተ ነው።

*ለኢትዮጵያ፣ ለኢትዮጵያዊነትና ለሰንደቅዓላማ*

*ቅሌታም ምሁራንን እናጋልጥ !*

*እንታገላቸው!*